በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የከተማ ልማትና ኮንስትራክሽን ሚኒስቴር
THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA
MINISTRY OF URBAN DEVELOPMENT & CONSTRUCTION

ቁጥር
Ref.No 8/0/00250/60
ቀን
Date 30/9/2011
አዲስ አበባ-ኢትዮጵያ
ADDIS ABABA - ETHIOPIA

757/2013

ቁ. 71/2011

ለክቡር አቶ ታዜር ገ/እንግዚአብሄር (ፕላንና መሬት ዘርፍ)
ለክቡር አቶ ካሊድ አብራህማን (የኮንስትራክሽን ዘርፍ)
ለክቡር አቶ መስፍን አሰፋ ካሳዬ (የከተማ ልማትና ቤቶች ዘርፍ)
ከ/ል/ኮ/ሚ/ር

ጉዳዩ፡- **የጸደቀ ግንኙነትና አሰራር መመሪያ ላይ የተደረገ ማሻሻያን ይመለከታል፣**

ሚኒስቴር መስሪያ ቤቱ እና ተጠሪ ተቋማት ሁሉም ስራዎች የጋራ አመራርን የሚመለከቱ መሆኑ እንደተጠበቀ ሆኖ ስራዎችን ለማሳለጥና ተቀናጅቶ ለመምራት ያስችል ዘንድ የግንኙነትና የአሰራር መመሪያ ተዘጋጅቶ ለሚኒካቢኔ አባላት ቀርቦ ውይይት ተደርጎበት መጽደቁ ይታወሳል፡፡ በዚህም መሰረት የጸደቀው መመሪያ ግንቦት 26 ቀን 2011 ዓ.ም በተጻፈ ማስታወሻ መላካችን ይታወቃል፡፡ ሆኖም ተጨማሪ ማሻሻያ ተደርጎበት ሰነዱ አባሪ ተደርጎ የተላከ መሆኑን እየገለጽኩ የሰነዱ ግልባጭ የተመዘገበላችሁም መመሪያውን እንድታስፈጽሙት አሳስባለሁ፡፡

ከሰላምታ ጋር

አይሻ መሐመድ ሙሳ (ኢንጅነር)
ሚኒስትር

ግልባጭ
- ለሚኒስትር ጽ/ቤት
- ለከተማ ልማትና ኮንስትራክሽን ሴክተር የፖሊሲ ጥናትና አማካሪ ቢሮ
- ለከተሞች መልካም አስተዳደር አቅም ግንባታ ቢሮ
- ለሰውጥና የሰው ሃብት ልማትና አስተዳደር ቢሮ
- ለከተሞች ገቢ ማሻሻያ፣ ፈንድ ሞብላይዜሽንና ፋይናንስ ቢሮ
- ለኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጂ ዳታ ቤዝ ልማት ቢሮ
- ለኮርፖሬትና ሀብት ስራ አመራር ቢሮ
- ለዕቅና ፕሮግራም በጀት ቢሮ
- ለመኖሪያ ቤቶች ልማትና አስተዳር ቢሮ
- ለከተማ መሬት ልማትና ማኔጅመንት ቢሮ
- ለከተማ ፕላን፣ ክትትልና ትግበራ ቢሮ
- ለከተሞች የአየር ንብረት ለውጥ ተጽዕኖ መቋቋሚያ ቢሮ
- ለኮንስትራክሽን ዘርፍ ተወዳዳሪነት ማበልጸጊያ ቢሮ
- ለኮንስትራክሽን ኢንዱስትሪ አሰራር ማሻሻያ ቢሮ
- ለኮንስትራክሽን ባለድርሻ አካላት ማስተባበሪያ ጽ/ቤት
- ለፌደራል ቤቶች ኮርፖሬሽን ጽ/ቤት
- ለኮንስትራክሽን ፕሮጀክት ማኔጅመንት ኢንስቲትዩት
- ለፌዴራል መሬትና መሬት ነክ ንብረት ምዝገባና መረጃ ኤጀንሲ
- ለፌደራል የከተሞች የሥራ ዕድል ፈጠራና የምግብ ዋስትና ኤጀንሲ
- ለኮንስትራክችን ስራዎች ቁጥጥር ባለሥልጣን
- ለመንግስት ህንጻ ግንባታ ፕሮጀክት ጽ/ቤት
- ለተቀናጀ የመሰረተ ልማት ማስተባበሪያ ኤጀንሲ
- ለሕዝብ ግንኙነትና ኮሙኒኬሽን ዳይሬክቶሬት
- ለኦዲት ዳይሬክቶሬት
- ለስነ-ምግባርና ጸረ ሙስና ዳይሬክቶሬት
- ለህግ አገልግሎት ዳይሬክቶሬት

ከ/ል/ኮ/ሚ/ር

ስልክ/ Tel
...4-12-71
...4-06-27
...4-12-84
...3-16-88

የፖ.ሳ.ቁ / P.O.Box
24134/1000

ፋክስ/ Fax
011-554-12-68
011-554-12-67

ድረ ገፅ / Web.site
www.mudc.gov.et
E-mail:PR.OFFICE@mudc.gov.et

# የከተማ ልማትና ኮንስትራክሽን ሚኒስቴር

## በየደረጃው የሚገኙ አካላት ስብሰባና የግንኙነት አሰራር መመሪያ ቁጥር 757/2013

ኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዴሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የአስፈጻሚ አካላትን ስልጣን ለመወሰን አዋጅ 1097/2011 አንቀጽ 22 መሰረት ለከተማ ልማትና ኮንስትራክሽን ሚኒስቴር የተሰጡትን ሥልጣንና ተግባራት በአግባቡ መወጣት እንዲችል በሚኒስቴሩ በየደረጃው የሚገኙ አካላት ተግባርና ኃላፊነታቸውን የሚወጡበትን የክትትልና የድጋፍ ሥርዓት መዘርጋት በማስፈለጉ ይህ የስብሰባና የግንኙነት አግባብ አሰራር መመሪያ ወጥቷል፡፡

### ክፍል አንድ

### ጠቅላላ

**አንቀጽ 1፡ አጭር ርዕስ**

ይህ መመሪያ "የከተማ ልማትና ኮንስትራክሽን ሚኒስቴር በየደረጃው የሚገኙ አካላት የስብሰባና የግንኙነት አሰራር መመሪያ ቁጥር 757/2013" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

**አንቀጽ 2፡ ትርጓሜ**

የቃሉ አገባብ ሌላ ትርጉም የሚያሰጠው ካልሆነ በስተቀር በዚህ መመሪያ ውስጥ፡-

1. "የሚኒስትሮች መድረክ" ማለት ሚኒስትር እና ሚኒስትር ዴኤታዎች በአባልነት እንዲሁም የሚኒስትር ጽ/ቤት ኃላፊ ያለ ድምጽ በፀሐፊነት የሚገኙበት አካል ነው፡፡
2. "የተቋም ማኔጅመንት ኮሚቴ" ማለት ሚኒስትር፣ ሚኒስትር ዴኤታዎች እና የተጠሪ ተቋማት ሃላፊና ምክትል ሃላፊዎች እንዲሁም የሚኒስትር ጽ/ቤት በጸሃፊነት የሚገኙበት አካል ነው፡፡
3. "የሚኒስትር መስሪያ ቤቱ ማኔጅመንት ኮሚቴ" ማለት ሚኒስትር፣ ሚኒስትር ዴኤታዎች፣ በሚኒስትር መስሪያ ቤቱ ዉስጥ የሚገኙ የቢሮ ሃላፊዎች፣ የጽ/ቤት ሃላፊዎች እና የሴቶች፣ህጻናትና ወጣቶች ዳይሬክተር፣የህዝብ ግንኙነት ዳይሬክተር፣ ኦዲት ዳይሬክተር፣የህግ አገልግሎት ዳይሬክተር በአባልነት እንዲሁም የዉሳኔ አፈጻጸም ክትትልና ድጋፍ ዳይሬክተር በጸሃፊነት የሚገኙበት አካል ነው፡፡

4. “የሚኒስትር ተጠሪ የሆኑ የሥራ ክፍሎች ማኔጀመንት ኮሚቴ” ማለት ለከተማ ልማትና ኮንስትራክሽን ሚኒስትር በቀጥታ ተጠሪ የሆኑ የሥራ ክፍሎች ኃላፊዎች እና ምክትል ሃላፊዎች በአባልነት የሚገኙበት አካል ነው፡፡
5. “የከተማ ልማትና ቤቶች ዘርፍ ማኔጅመንት ኮሚቴ” ማለት ለከተማ ልማትና ቤቶች ዘርፍ ሚኒስትር ዴኤታ በቀጥታ ተጠሪ የሆኑ የሥራ ክፍሎች ኃላፊዎች እና ምክትል ሃላፊዎች በአባልነት የሚገኙበት አካል ነው፡፡
6. “የፕላንና መሬት ዘርፍ ማኔጅመንት ኮሚቴ” ማለት ለፕላንና መሬት ዘርፍ ሚኒስትር ዴኤታ በቀጥታ ተጠሪ የሆኑ የሥራ ክፍሎች ኃላፊዎች እና ምክትል ሃላፊዎች በአባልነት የሚገኙበት አካል ነው፡፡
7. “የኮንስትራክሽን ዘርፍ ማኔጅመንት ኮሚቴ” ማለት ለኮንስትራክሽን ዘርፍ ሚኒስትር ዴኤታ በቀጥታ ተጠሪ የሆኑ የሥራ ክፍሎች ኃላፊዎች እና ምክትል ሃላፊዎች በአባልነት የሚገኙበት አካል ነው፡፡
8. “የሥራ ክፍሎች ማኔጅመንት ኮሚቴ” ማለት በሚኒስቴሩ ውስጥ በሚገኙ በእያንዳንዱ ቢሮና ዳይሬክቶሬቶች ሥር የተደራጁ የሥራ ክፍል ኃላፊዎች እና የልማት ቡድን ሰብሳቢ በአባልነት የሚገኙበት አካል ነው፡፡
9. በዚህ መመሪያ በወንድ ጾታ የተገለጸው የሴትንም ጾታ ይጨምራል፡፡

ንቀጽ 3፡ ዓላማ

ዚህ መመሪያ ዓላማ በሚኒስቴሩ ውስጥ በየደረጃው የሚገኙ አካላት የሚኒስቴሩን ተልዕኮ፣ ተግባርና ኃላፊነት ለመፈጸም የሚያስችል ዕቅድ ለማዘጋጀት፣ ክትትል፣ ድጋፍና ግምገማ ማድረግ እና ሪፖርት ለማቅረብ የሚያስችሉ የስብሰባና የግንኙነት አግባቦችን መደንገግ ነው፡፡

ንቀጽ 4፡ የተፈጻሚነት ወሰን

ዚህ መመሪያ በሚኒስትሮች መድረክ፣ በማኔጅመንት ኮሚቴ፣ የከተማ ልማትና ቤቶች ዘርፍ ማኔጅመንት ኮሚቴ፣ የፕላንና መሬት ዘርፍ ማኔጅመንት ኮሚቴ፣ የኮንስትራክሽን ዘርፍ ማኔጅመንት ኮሚቴ እና የሥራ ክፍሎች ማኔጅመንት ኮሚቴ ስብሰባና የግንኙነት አግባብ ላይ ተፈጻሚ ይሆናል፡፡

## ክፍል ሁለት

## የሚኒስትሮች መድረክ

ንቀጽ 5፡ መደበኛ ስብሰባ

የሚኒስትሮች መድረክ በየሳምንቱ ሰኞ ከቀኑ 3፡00 ሰዓት ጀምሮ ይካሄዳል። ሆኖም አስቸኳይ አጀንዳ ሲኖር በማንኛውም ቀንና ሰዓት በሚኒስትር ሊጠራ ይችላል።

የሚኒስትሮች መድረክ የሚመራው በሚኒስትር ነው። ሆኖም ሚኒስትር በማይኖርበት ጊዜ በተለይ ውክልና ካልተሰጠ በስተቀር በሹመት ቅድሚያ ያለው ሚኒስትር ዴኤታ ይመራል።

ንቀጽ 6፡ የሚኒስትሮች መድረክ የሚያተኩርባቸው ጉዳዮች

በዘርፎች ተጠቃለው የቀረቡ ዕቅዶችና ሪፖርቶች፣ ረቂቅ ሕጎች፣ ፖሊሲዎችና ስትራቴጂዎች ለማኔጅመንት ኮሚቴ ከመቅረባቸው በፊት የሀገሪቱን የዕድገትና ትራንስፎርሜሽን ዕቅድ እና ወቅታዊ ሁኔታን በመከተል መዘጋጀታቸውን ያረጋግጣል።

በማኔጅመንት ኮሚቴ የጸደቁ ዕቅዶችና ሪፖርቶች፣ ረቂቅ ሕጎች፣ ፖሊሲዎችና ስትራቴጂዎች ለሚመለከታቸው የመንግሥት አካላት ከመላካቸው በፊት አቀራረባቸውና ይዞታቸው አግባብ መሆኑን መርምሮ ያረጋግጣል።

በሚኒስቴሩ ሥር የተደራጁ የተለያዩ ዘርፎች የዕቅድ አፈጻጸም ያለበትን ሁኔታና ያጋጠሙ ችግሮችን መርምሮ የመፍትሔ አቅጣጫዎችን ያስቀምጣል።

ለማኔጅመንት ኮሚቴ የሚቀርቡ አጀንዳዎችን አግባብነት መርምሮ ውሳኔ ይሰጣል።

በሚኒስቴሩ የሚካሄዱ የተለያዩ ስብሰባዎች፣ ጉባኤዎች፣ ወርክሾፖችና ኮንፈረንሶች መርሐግብር፣ አጀንዳ፣ ወዘተ … መርምሮ ውሳኔ ይሰጣል።

ንቀጽ 7፡ የተቋም ማኔጅመንት ኮሚቴ የስብሰባና የግንኙነት አሰራር

የማኔጅመንት ኮሚቴ መደበኛ ስብሰባ ማክሰኞ በየ15 ቀን ከቀኑ 3፡00 ሰዓት ጀምሮ ይካሄዳል። ሆኖም አስቸኳይ አጀንዳ ሲኖር በማንኛውም ጊዜ በሚኒስትር ሊጠራ ይችላል።

የማኔጅመንት ኮሚቴ ስብሰባ የሚመራው በሚኒስትር ነው። ሆኖም ሚኒስትር በማይኖርበት ጊዜ በተለይ ውክልና ካልተሰጠ በስተቀር በሹመት ቅድሚያ ባለው ሚኒስትር ዴኤታ ይመራል።

ንቀጽ 8፡ የተቋም ማኔጅመንት ኮሚቴ ስብሰባ የሚያተኩርባቸው ጉዳዮች

. የማኔጅመንት ኮሚቴ ስብሰባ ትኩረት የሚሰጥባቸው ጉዳዮች በሚኒስትሮች መድረክ በአጀንዳነት እንዲያዙ፣ ውሳኔ ያገኙ፣ በዘርፍ ደረጃ የጸደቁ የሴክተሩ ረቂቅ ፖሊሲዎች፣ ስትራቴጂዎች፣ ሕጎች እንዲሁም ዕቅዶች፣ፕሮግራሞች፣ፕሮጀክትና ሪፖርቶች ናቸው።

2. ለማኔጅመንት ኮሚቴ የሚቀርቡ ጉዳዮችና ወቅታዊ የሥራ አፈፃፀም በሚመለከተው ዘርፍ የሥራ ክፍል አስፈላጊው ዝግጅት ተደርጎ በሰነድና በፓወር ፓይንት መቅረብ አለባቸው።

ንቀጽ 9፡- የሚኒስትር መስሪያቤቱ ማኔጅመንት ኮሚቴ የስብሰባና የግንኙነት አሰራር

1. የሚኒስትር መስሪያ ቤቱ ማኔጅመንት ኮሚቴ መደበኛ ስብሰባ በየወሩ በበላይ አመራሩ በሚወሰን ቀንና በተመረጡ አጀንዳዎች ላይ ይካሄዳል። ሆኖም አስቸኳይ አጀንዳ ሲኖር በማንኛውም ጊዜ በሚኒስትር ሊጠራ ይችላል።

2. የሚኒስትር መስሪያ ቤቱ ማኔጅመንት ኮሚቴ ስብሰባ የሚመራው በሚኒስትር ነው። ሆኖም ሚኒስትር በማይኖርበት ጊዜ በተለይ ውክልና ካልተሰጠ በስተቀር በሹመት ቅድሚያ ባለው ሚኒስትር ዴኤታ ይመራል።

ንቀጽ 10፡- ዶክሜንቴሽን

. የሕዝብ ግንኙነትና ኮሚኒኬሽን ዳይሬክቶሬት ዳይሬክተር የማኔጅመንት ኮሚቴ ስብሰባዎችን ቃለ-ጉባኤ አደራጅቶ ይይዛል።

. የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) እንደተጠበቀ ሆኖ የሕዝብ ግንኙነት ዳይሬክቶሬት የማኔጅመንት ኮሚቴ ስብባዎችን በቪዲዮ፣ በኦዲዮና በፎቶግራፍ ቀርጾ ሊይዝ ይችላል።

. ማንኛውም ቃለ-ጉባኤ በሕዝብ ግንኙነት ዳይሬክቶሬት አማካይነት በዘመናዊ የሰነድ አያያዝ ሥርዓት በጥንቃቄ ይያዛል።

. በቃለ-ጉባኤ የተላለፉ ውሳኔዎች እንደ አስፈላጊነታቸው ለአፈጻጸም ለሚመለከተው መመራት አለባቸው።

ንቀጽ 11፡- ውሳኔዎችን ስለማስፈጸም

. በማኔጅመንት ኮሚቴ የተላለፉ ውሳኔዎች በሚመለከታቸው አካላት እንዲፈጸሙ በሚኒስትር ጽ/ቤት ኃላፊ አማካይነት ለሚመለከታቸው ይተላለፋሉ።

* የከተማ ልማትና ኮንስትራክሽን * ... ማህደር የሥራ ሂደት

2. የሚኒስትር ጽ/ቤት ኃላፊ ከሚመለከተው ዘርፍ ጋር እየተመካከረ የማኔጅመንት ኮሚቴ ውሳኔዎች አፈጻጸም ያለበትን ደረጃ በመከታተል ለሚኒስትሮች መድረክ ሪፖርት ማቅረብ አለበት፡፡

## ክፍል ሦስት

## የዘርፍ ማኔጅመንት ኮሚቴ

### አንቀጽ 12፡- የዘርፍ ማኔጅመንት ኮሚቴ

በዚህ መመሪያ የሚከተሉት የዘርፍ ማኔጅመንት ኮሚቴዎች ተመስርተዋል፡-

1. ለሚኒስትር ተጠሪ የሆኑ የሥራ ክፍሎች፤
2. ለከተማ ልማትና ቤቶች ዘርፍ ሚኒስትር ዴኤታ በቀጥታ ተጠሪ የሆኑ የሥራ ክፍሎች፤
3. ለፕላንና መሬት ዘርፍ ሚኒስትር ዴኤታ ተጠሪ የሆኑ የሥራ ክፍሎች፤
4. ለኮንስትራክሽን ዘርፍ ሚኒስትር ዴኤታ ተጠሪ የሆኑ የሥራ ክፍሎች ኃላፊዎች በአባልነት የሚገኙባቸው አካላት ናቸው፡፡

### አንቀጽ 13፡- የዘርፍ ማኔጅመንት ኮሚቴዎች ተግባርና ሃላፊነት

1. የዘርፉን ዕቅድ መርምሮ ያጸድቃል፤
2. የዘርፉ ዕቅድ አፈጻጸም ያለበትን ደረጃ ይከታተላል፤ ይቆጣጠራል፤ ለፈጻሚዎች ድጋፍ ይሰጣል፡፡
3. የአፈጻጸም ክፍተት የሚታይባቸውን የሥራ ክፍሎች ለይቶ ተገቢው እርምጃ እንዲወሰድ ውሳኔ ያስተላፋል፡፡
4. በዘርፉ የሚስተዋሉ የመልካም አስተዳደር ችግሮችን ይለያል፤ የመፍትሔ እርምጃዎችን በተመለከተ ውሳኔ ይሰጣል፡፡
5. ለማኔጅመንት ኮሚቴ መቅረብ የሚገባቸውን የዘርፉን ዕቅዶች፣ ፕሮግራሞች ፣ፕሮጀክትና ሪፖርቶች መርምሮ ያጸድቃል፡፡
6. ለማኔጅመንት ኮሚቴ የሚቀርቡ የዘርፉን ፖሊሲዎች፣ ስትራቴጂዎችና ሕጎች መርምሮ ያጸድቃል፡፡

**አንቀጽ 14፡- <u>የዘርፍ ማኔጅመንት ኮሚቴዎች የስብሰባ ሥነሥርዓት</u>**

1. የየዘርፉ የማኔጅመንት ኮሚቴዎች የየራሳቸው የስብሰባ ቀን፣ ሰዓትና ሥነሥርዓት ይኖራቸዋል። ሆኖም የተቀናጀ አሰራር ለማስፈን ሲባል የየዘርፉ ማኔጅመንት ኮሚቴዎች መደበኛ ስብሰባ በየ15 ቀን ሐሙስ ከጧቱ 3፡00 ሰዓት ጀምሮ ይካሄዳል።
2. የዘርፍ የማኔጅመንት ኮሚቴዎች ቃለጉባኤ በዘርፉ ሚኒስትር ዴኤታ ልዩ ረዳቶች የሚያዝ ይሆናል።

**አንቀጽ 15፡ <u>የውሳኔዎች አፈጻጸም</u>**

ማንኛውም በዘርፍ ማኔጅመንት ኮሚቴ የተላለፉ ውሳኔዎች ከመፈጸማቸው በፊት ለሚኒስትሮች መድረክ ቀርበው መጽደቅ አለባቸው።

## <u>ክፍል አራት</u>

## <u>የሥራ ክፍሎች ማኔጅመንት ኮሚቴ</u>

**አንቀጽ 16፡ <u>የሥራ ክፍሎች ማኔጅመንት ኮሚቴዎች</u>**

1. እያንዳንዱ ቢሮና በዳይሬክቶሬት ደረጃ የሚገኙ የሥራ ክፍሎች የቢሮ/ዳይሬክቶሬቱ ቢሮ ኃላፊ/ዳይሬክተር እና የለዉጥ ቡድን ኃላፊዎች በአባልነት የሚገኙበት የሥራ ክፍሎች ማኔጅመንት ኮሚቴ ይኖራቸዋል።
2. የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) እንደተጠበቀ ሆኖ የሚመለከተው ሚኒስትር ወይም ሚኒስትር ዴኤታ አግባብነት ያላቸው ግንባር ቀደም ሠራተኞች የሥራ ክፍሎች ማኔጅመንት ኮሚቴ አባል እንዲሆኑ ሊያደርግ ይችላል።

**አንቀጽ 17፡ <u>የሥራ ክፍሎች ማኔጅመንት ኮሚቴዎች ተግባርና ሃላፊነት</u>**

1. ማንኛውም የሥራ ክፍል ማኔጅመንት ኮሚቴ በአጠቃላይ የሚኒስቴሩን እና በተለይ የሚገኝበትን ቢሮ/ዳይሬክቶሬት ተልዕኮ ለማሳካት በሚያስችል ቁመናና ዝግጅት ላይ የተገነባ እንዲሁም በአመለካከት፣ በክህሎትና በሥነ ምግባር የታነጸ ሞዴል ሠራተኛ ለመፍጠር አቅዶ መስራት፤
2. በቢሮ/ዳይሬክቶሬቱ የሙስናና የፀረ ኪራይ ሰብሳቢነት አመለካከት ትግሉን በጽናት ማስቀጠል እና ሴክተሩ የሚሰጠውን ተልዕኮ በብቃትና በላቀ ውጤት መፈጸም፤
3. የቢሮ/ዳይሬክቶሬቱ ሠራተኞች በለውጥ አጀንዳ ተነሳስተው ለሥራ እንዲተጉ ማድረግ፤ ሠራተኞች በሥራ ውጤታቸው እንዲመዘኑ ማድረግ፤

4. ከሚኒስቴሩ ዕቅድ በመነሳት በየምዕራፍ የሚያከናውናቸውን ተግባራት በግልጽ በማስቀመጥ የአመራር ሉደትን በመጠበቅ መንቀሳቀስ፤
5. የሪፎርም ማስፈፀሚያ መሳሪያዎች በአግባቡ ሥራ ላይ መዋላቸውን ማረጋገጥ፣ የውጤት ተኮር ምዘና ሥርዓቱ እስከ ግለሰብ ድረስ በአግባቡ ተግባራዊ መሆኑን መከታተል፤
6. በቢሮ/ዳይሬክቶሬቱ የሚታዩ ክፍተቶችን በየጊዜው በመለየት እንዲስተካከሉ ማድረግ፤ ስለተግባራዊነቱ ማረጋገጥ፣ ለተደራጀበት ዘርፍ የበላይ አመራር ማስታወቅ፤
7. በቢሮ/ዳይሬክቶሬቱ ሥር የሚገኙ ሠራተኞች በአመለካከትና በአስተሳሰብ የተለወጡ፣ በእውቀታቸውና በክህሎታቸው የላቀ ብቃት ኖሯቸው ተልዕኳቸውን በተሟላ ሁኔታ መፈፀም እንዲችሉ በመደገፍ የውጤትና የብቃት ደረጃቸው ወደ ሌሎች እንዲሰፋ ማድረግ፤
8. የቢሮ/ዳይሬክቶሬቱን ሠራተኞች የአመለካከትና የክህሎት ክፍተቶች በማጥናት የአቅም ግንባታ ሥልጠና እንዲያገኙ ከሚመለከታቸው አካላት ጋር ግንኙነት መፍጠር፤
9. በሥራ ሂደቱ ቀልጣፋና ውጤታማ አገልግሎት እየተሰጠ መሆኑን ማረጋገጥ፤ በሚገኝበት ቢሮ/ዳይሬክቶሬት መልካም አስተዳደር እንዲሰፍን ማድረግ፤
10. በምዘና ስርዓቱ የተሻሉ ፈፃሚዎች በየጊዜው እየተለዩ የሚበረታቱበትን ሁኔታ ማመቻቸት፤ በሥራ ውጤታቸው የደከሙ ሠራተኞች የሚደገፉበትን ሁኔታ ማመቻቸት፤

## ክፍል አምስት

## ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች

### አንቀጽ 18፡ ምልዓተ-ጉባኤ

1. ማንኛውም የሚኒስትሮች፣ የተቋም ማኔጅመንት ኮሚቴ፣የሚኒስትር መስሪያ ቤቱ ማኔጅመንት ኮሞቴ፣ የዘርፍ ማኔጅመንት ኮሚቴ እና የሥራ ክፍሎች ማኔጅመንት ኮሚቴ አባላት የስብሰባውን ቀንና ሰዓት አክብረው መገኘት አለባቸው፡፡ መገኘት ከሚገባቸው አባላት 2/3 ከተገኙ ምልዓተ ጉባኤ ይሆናል፡፡
2. በበላይ አመራሩ በታመነ ምክንያት ወይም ከአቅም በላይ በሆነ ሁኔታ የማይገኝ አባል አግባብነት ያለው ተወካይ መላክ አለበት፡፡

3. ማንኛውም የስብሰባው ተሳታፊ አባል ስብሰባው የተጠራበትን ርዕስ ጉዳይ በተመለከተ አስፈላጊውን ዝግጅት አድርጎ መገኘት ይጠበቅበታል፡፡

## አንቀጽ 19፡ የውሳኔ አሰጣጥ

የማንኛውም አካል ውሳኔ የሚተላለፈው በተባበረ ድምጽ ነው፡፡ ሆኖም በተባበረ ድምጽ መወሰን ካልተቻለ አብላጫ ድምጽ ያለው ወገን ሃሳብ ያልፋል፡፡ ድምጽ እኩል ከሆነ ግን ሰብሳቢው የደገፈው ወገን ድምጽ ያልፋል፡፡

## አንቀጽ 20፡ ተጠያቂነት

ማንኛውም የሚኒስትሮች፣ የተቋም ማኔጅመንት ኮሚቴ፣የሚኒስትር መስሪያ ቤቱ ማኔጅመንት ኮሞቴ፣ የዘርፍ ማኔጅመንት ኮሚቴ እና የሥራ ክፍሎች ማኔጅመንት ኮሚቴ አባላት የስብሰባውን ቀንና ሰዓት አክብረው መገኘት አለባቸው፡፡ ሆኖም ይህንን የአሰራር ስርዓት መመሪያ እንዳይፈጸም ያደረገ አካል ተጠያቂ ይሆናል፡፡

## አንቀጽ 21፡ መመሪያውን ስለማሻሻል

ይህ መመሪያ አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ በማንኛውም ጊዜ ሊሻሻል ይችላል፡፡

## አንቀጽ 21፡ መመሪያው የሚጸናበት ጊዜ

ይህ መመሪያ በበላይ አመራሩ ከፀደቀበት ግንቦት 26 ቀን 2011 ዓ.ም ጀምሮ የጸና ይሆናል፡፡

አይሻ መሐመድ ሙሳ (ኢንጂነር)

ሚኒስትር

# አባሪ

# የከተማ ልማትና ኮንስትራክሽን ሚኒስቴር የሥራ ክፍሎችና ተጠሪ ተቋማት

## የዘርፍ አደረጃጀት

1. ለሚኒስትር ተጠሪ የሆኑ የሥራ ክፍሎች
    1.1. የሚኒስትር ጽ/ቤት
    1.2. የከተማ ልማትና ኮንስትራክሽን ሴክተር የፖሊሲ ጥናትና አማካሪ ቢሮ
    1.3. እቅድና በጀት ቢሮ
    1.4. የከተሞች ገቢ ማሻሻያ፣ ፈንድ ሞቢላይዜሽንና ፋይናንስ ቢሮ
    1.5. የኮርፖሬት ሀብት ስራ አመራር ቢሮ
    1.6. የኮንስትራክሽ ሥራዎች ቁጥጥር ባለስልጣን (ተጠሪ ተቋም)
    1.7. ለሕዝብ ግንኙነትና ኮሙዩኒኬሽን ዳይሬክቶሬት
    1.8. ኦዲት ዳይሬክቶሬት
    1.9. ለሕዝብ ግንኙነትና ኮሙዩኒኬሽን ዳይሬክቶሬት
    1.10. የስነ ምግባርና ጸረ- ሙስና ዳይሬክቶሬት

2. ለፕላንና መሬት ዘርፍ ሚኒስትር ዴኤታ ተጠሪ የሆኑ የሥራ ክፍሎች
    2.1. የከተማ ፕላን ዝግጅትና ትግበራ ክትትል ቢሮ
    2.2. የከተማ መሬት ልማትና ማኔጅሜንት ቢሮ
    2.3. የኢንፎርሜሽን ቴክኖሎኖጂና ዳታቤዝ ልማት ቢሮ
    2.4. የፌደራል መሬትና መሬት ነክ ምዝገባ ኤጀንሲ (ተጠሪ ተቋም)
    2.5. የለዉጥ፣የሰዉ ሃብትና አስተዳደር ቢሮ

3. ለኮንስትራክሽን ዘርፍ ሚኒስትር ዴኤታ ተጠሪ የሆኑ የሥራ ክፍሎች
    3.1. የኮንስትራክሽን ዘርፍ ተወዳዳሪነት ማበልጸጊያ ቢሮ
    3.2. የኮንስትራክሽን ኢንዱስትሪ አሰራር ማሻሻያ ቢሮ
    3.3. የኮንስትራክሽን ባለድርሻ አካላት ማስተባበሪያ ጽ/ቤት
    3.4. የመንግስት ህንጻ ግንባታ ፕሮጀክት ጽ/ቤት
    3.5. ፕሮጀክት ማኔጅመንት ኢንስቲትዩት (ተጠሪ ተቋም)

4. ከተማ ልማትና ቤቶች ዘርፍ ሚኒስትር ዴኤታ ተጠሪ የሆኑ የሥራ ክፍሎች
    4.1. የመኖሪያ ቤቶች ልማት እና አስተዳደር ቢሮ
    4.2. የከተሞች መልካም አስተዳደርና አቅም ግንባታ ቢሮ
    4.3. የከተሞች የአየር ንብረት ለውጥ ተጽዕኖ መቋቋሚያ ቢሮ
    4.4. የተቀናጀ የመሰረተ ልማት አገልግሎት ኤጀንሲ (ተጠሪ ተቋም)
    4.5. የፌደራል የከተሞች ሥራ ዕድል ፈጠራና ምግብ ዋስትና ኤጀንሲ (ተጠሪ ተቋም)
    4.6. የፌደራል ቤቶች ኮርፖሬሽን (ተጠሪ ተቋም) ናቸው፡፡